# በአሲምባ ደኖችም ባለታሪክ ናቸው

*መብራቱ ይበልህ /ከኢዜአ/*
*ዜና ሐተታ*

ደኖች እርጥበትን በመያዝና ድርቅን በመከላከል በቀላሉ የማይገመት ሚና አላቸው።አንዲት ሀገር የደን ሀብቷ በአግባቡ የተጠበቀ ከሆነ በዘርፉ ለምታገኘው አጠቃላይ ገቢ ወይም ጂዲፒ የራሱ ድርሻ አለው።ኢትዮጵያ ከአራት አስርት ዓመታት በፊት ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ከ40 በመቶ ያላነሰው በደን የተሸፈነ እንደነበር ታሪክ ያስታውሰናል።ይህ ሰፊ እምቅ ሀብት ግን ብዙም ሳይቆይ ተመናምኖ በአሁኑ ወቅት 3 ከመቶ ያልዘለለ ደን ቀርቷል።ይህ በራሱ የመጣ ክስተት አይደለም። በግንዛቤ እጥረትም ይሁን የራስን ጥቅም በማሰብ ብቻ ልዩ ልዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ባደረጉት የጥፋት ርብርቦሽ እንጂ።

ይሁንና በአንዳንድ የሀገሪቱ ክልሎች በሚገኙ ተራራማና ስምጥ ሸለቆዎች በአካባቢው ነዋሪዎች ብርቱ ተጋደሎ ተጠብቀው የቆዩ ደኖች ዛሬም ድረስ ምስክር ናቸው።አቶ ንጉሴ ሱባ የኢሮብ ተወላጅ ናቸው።ትውልዳቸው በአሲምባ ተራራ ስር በመሆኑ ስለ አሲምባ ማንነት ጠንቀቀው ያውቃሉ።አሲምባ በትግራይ ምሥራቃዊ ዞን በኢሮብ ወረዳ የሚገኝ ተራራ ነው።እዚህ ስፍራ ላይ ኢህአፓ ደርግን ለመፋለም መሽጋበታለች።ፋሽስቱ ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅትም በርካታ የጸረ ቅኝ ግዛት አርበኞች መከታ ሆኗቸው ቆይቷል።

በተጨማሪም ለረጅም ዘመናት የተፈጥሮ ደን ተጠብቆ የቆየበት ሥፍራ መሆኑን በትዝታ ይናገራሉ። በትግራይ ቀደምት የነበሩ የተፈጥሮ ዛፎችና የዱር እንስሳት ለምስክርነት በዓሲምባ ተራራ መቅረታቸውን ነው አቶ ንጉሴ የሚገልጹት።የሀበሻ ጥድ፣ ወይራ፣ ክትክታ፣ ግራርና ሌሎች ቁጥር ስፍር የሌላቸው የዛፍ ዓይነቶችን አሲምባ በውስጡ አቅፎ ይዟል። በርካታ የዱር እንስሳትና አእዋፋትንም እንዲሁ።

አቶ አብራሃ ሕሉፍ በደቡባዊ ዞን በሕንጣሎ ዋጅራት ወረዳ ወጅግ ማሕጎ_ዋረን ከተባለ የተፈጥሮ ደን ኩታገጠም በሆነው አንዱ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ተወልደው ያደጉ ናቸው።ወጅግ ማሕጎ_ዋረን የተፈጥሮ ደን ከአጼ ኃይለሥላሴ መንግስት ጀምሮ ህብረተሰቡ በራሱ አነሳሽነት ሌሊትም ቀንም በመጠበቅ ለአሁኑ ትውልድ ማስረከቡን ነው የሚናገሩት።።

የትግራይ ብሄራዊ ክልላዊ ምክር ቤት መጋቢት አጋማሽ ላይ ባካሄደው መደበኛ ጉባኤ ለበርካታ ዓመታት ህብረተሰቡ ሲጠብቃቸውና ሲንከባከባቸው የቆየውን የዓሲምባ ጉንዳጉንዶ፣የውጅግ ማሕጎ_ዋረንና የደብረዓባይና ዱጋድጉኚ ተፈጥሮ ደኖች የክልሉ መንግሥት ተረክቦ እንዲያስተዳድራቸው ወስኗል።ለዓመታት ህብረተሰቡ ሲጠይቀው የነበረው ጉዳይ ምላሽ በማግኘቱ ነዋሪዎቹ ደስታቸው ወሰን አልነበረውም ይላሉ አቶ ንጉሴ።ሶስቱም የተፈጥሮ ደኖች ስፋታቸው 115 ሽህ 605 ሄክታር መሬት የሚሸፍን

ነው። በውስጣቸውም በርካታ ተሳቢና አእዋፋት፣ሰስ፣ ሚዳቋና ሌሎች የዱር እንስሳት መኖሪያ መሆናቸውን የደን ባለሙያው አቶ ብርሃኑ መረሳ ጠቁመዋል።

የክልሉ መንግስት ባለፈው ዓመትም በደቡባዊና ሰሜን ምእራብ የሚገኙ የሕጉም ቡርዳ፣ግራ ካሕሱና ሕርሚ የተባሉ ሁለት የተፈጥሮ ደኖችን ለማስተዳደር መወሰኑን ገልጸዋል።የተፈጥሮ ደኖቹ ስፋት 52 ሽህ 551 ሄክታር መሬት መሆኑንም ይናገራሉ።በተለይም የተከዜ ወንዝ የሕርሚ ተፈጥሮ ደንን  አቋርጦ የሚፈስ በመሆኑ የበርካታ ብዝሃ ህይወት መፍለቂያ መሆኑንም ያስረዳሉ።

ይህንኑ የበለጠ ለማጠናከር በትግራይ ክልል በየዓመቱ ከ1ነጥብ 4 ሚሊዮን በላይ ህዝብ በተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ስራ ላይ ይሰማራል።ይህም ቀደም ሲል በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ያጠፋውን የተፈጥሮ ደን መልሶ ወደነበረበት ለመመለስ ነው ይላሉ። በዚህም ሰፋፊ ተፋሰሶችና ተራራዎች ለምተዋል።በ14ኛው ክፍለ ዘመን እንደተቆረቆረ የሚነገርለት የማሪያም ጉንዳ ጉንዶ ደብር በህብረተሰቡ ጥያቄ በደኑ ክልል ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል።የአካባቢው ህብረተሰብ ከደኑ ተጠቃሚ እንዲሆን ደንብና መመሪያ በመዘጋጀት ላይ መሆኑንም ባለሙያው ጠቁመዋል።

በመሆኑም ክልሉ የአምስት የተፈጥሮ ደኖችን ጨምሮ በፌደራል የሚተዳደሩ የቃፍታ ሽራሮ ብሄራዊ ፓርክና የዴስአ ተፈጥሮ ደን ባለቤት ለመሆን በቅቷል።በዚህም የክልሉ ገፅታ እየተቀየረ ነው።ለዚህ ደግሞ የትግራይ ክልል አርሶአደሮች የአንበሳውን ድርሻ ይይዛሉ።ለረጅም ዘመናት ተራቁቶ የቆየውን አካባቢያቸውን ዛሬ ወደነበረበት እንዲመለስ አድርገውታል።የአሲምባ ተራራም ደኖች ሁሉ ሽሽተው በጠፉበት ወቅት ብቸኛ ምስክርና ባለታሪክ ሆኖ ተገኝቷል።ስለሆነም በአሲምባ ደኖችም ባለታሪክ ናቸውና ይጠበቁ እንላለን።ቸር ይግጠመን።

---END---